የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/1482/14
ቀን/Date ሚያዚያ 07 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመሠረታዊ ሸቀጦች ቀረጥና ታክስ ይመለከታል፤</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/5340 ቀን 06/8/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እየተፈቀደ እንዲገባ በቀን 30/7/2014 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/5302 በተጻፈ ደብዳቤ መፈቀዱን በማስታወስ በደብዳቤው ላይ ቀረጥና ታክሱን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 22/3/2013 በቁጥር ማኢ.30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም ተብሎ የተገለፀው ተሰርዞ በ28/12/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/1431 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም ተብሎ የተስተካከለ መሆኑን አሳውቋል፡፡

ቀደም ሲል የገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 30/7/2014 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/5302 ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ እንዲደረግ ከኮሚሽኑ በቁጥር 4/1476/14 ሚያዚያ 04 ቀን 2014 በተጻፈ ደብዳቤ መገለጹ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በላከው ማስተካከያ መሠረት የመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦቹ የቀረጥና ታክስ አከፋፈል በተመለከተ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ22/3/2013 በቁጥር ማኢ.30/7/51 በተጻፈ ደብዳቤ በተላለፈው ደብዳቤ ሳይሆን በ28/12/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/1431 በተጻፈው ደብዳቤ አግባብ ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳወቀበትን 02 ገጽ እንዲሁም ቀደም ሲል ከኮሚሽኑ የተላለፈውን ደብዳቤ 08 ገጽ በድምሩ 10 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሙሉጌታ በየነ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር
ተወካይ

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢፌዴሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ለኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

**ጉምሩክ ኮሚሽን**

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

**በያሉበት፣**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር / Ref.No ሚኢ30/7/5340

ቀን / Date 6/8/2014

ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የመሠረታዊ ሸቀጦች ቀረጥና ታክስ ይመለከታል፤

በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እየተፈቀደ እንዲገባ በቀን 30/7/2014 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/5302 በተጻፈ ደብዳቤ መፈቀዱ ይታወሳል::

በደብዳቤው ላይ ቀረጥና ታክስሱን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/3/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም ተብሎ የተገለጸው ተሰርዞ በ28/12/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/1431 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም ተብሎ የተስተካከለ መሆኑን እየገለጽን፤ ከዚህ ጋር ደብዳቤውን 1 ገጽ አባሪ አድርገን ልከናል::

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
አዲስ አበባ

ስልክ
251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81፡ 83 86 89

የፖ.ሣ.ቁ
P.O.BOX 1905,1037

ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96

MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ሚገ22/ገ/1431
Ref. No.

ቀን 28/12/2013
Date

ለገቢዎች ሚኒስቴር

ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ለጉምሩክ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ቀረጥና ታክስ ላይ የተደረገ ማሻሻያ፤</u>

በመሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ላይ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ግሽበት ለማረጋጋት እንዲሁም አሁን ካለበት ዋጋ መቀነስ እንዲቻል፡-

1. ስንዴ ከውጭ ሲገባ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆን፤
2. የምግብ ዘይት ከውጭ ሲገባም ሆነ በአገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምበት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆን፤
3. በታሪፍ ቁጥር 1701.1200፣ 1701.1390፣ 1701.1400 እና 1701.9900 የሚመደበው ስኳር ከውጭ ሲገባም ሆነ በአገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምበት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆን፤
4. ሩዝ ከውጭ ሲገባም ሆነ በአገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምበት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሆን፤
5. ፓስታ እና ማክሮኒ ከውጭ ሲገባም ሆነ በአገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምበት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ እንዲሆን፤
6. የዶሮ እንቁላል ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እንዲሆን፤

ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ተቀባይነት በሚያገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖች ላልተወሰነ ጊዜ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነ መሆኑን እንገልጻለን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከዓላማው አንጻር አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ እናሳስባለን።

Ministry of Finance ARCHIVE 6

4/1476/14

ሚያዝያ 0 4 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመሠረታዊ ሸቀጦች ቀረጥና ታክስ ይመለከታል</u>፤

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/5302 ቀን 30/7/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ወተት እና ሩዝ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮቫሉታ) ለስድስት ወራት ምንጩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እየተረጋገጠ እንዲገቡ በቀን 7/8/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/108 በተጻፈ ደብዳቤ መፈቀዱን በማስታወስ በአሁኑ ጊዜ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት እንዲቻል እና በርካታ የውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የራሳቸውን አወንታዊ ሚና መጫወት እንዲችሉ የፍራንኮቫሉታ ፈቃድ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ እያቀረቡ በመሆኑ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ዱቄት ወተት እና ሩዝ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እየተፈቀደ እንዲገባ መንግስት መወሰኑን በመግለጽ ቀረጥና ታክሱን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/03/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም፤ አፈጻጸሙን በሚመለከት በሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት አሳስቧል።

በዚሁ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ መሠረት፡-

1. መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚፈልጉ የውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በደብዳቤ ሲረጋገጥ፤

2. አስመጪዎቹ በዘርፉ የታደሰ የአስመጪነት ፈቃድ ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የአስመጪነት ንግድ ፈቃድ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፤

3. መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር እንዲያስገባ ፈቃድ ያገኘ እና ዲክለር ያደረገ አስመጪ የትራንዚት ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ዕቃዎቹን አጠቃሎ በሶስት ወራት ጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሀገር አስገብቶ ማጠናቀቅ እንዳለበት፤

4. አንድ አስመጪ በአንድ የግዥ ሰነድ /Commercial Invoice/ ግዥ የፈጸመባቸውን የምግብ ሸቀጦች በአንድ ዲክላራሲዮን መዝግቦ አስመጪው በመረጠው በአንድ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የምግብ ሸቀጦቹን አጠቃሎ ወደ ሀገር ማስገባት እንደሚጠበቅበት፤

5. ከላይ በተገለፀው አግባብ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገባ የትራንዚት ፈቃድ ያገኘ አስመጪ ለሁለተኛ ጊዜ /በድጋሚ/ የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ለማስገባት ከፈለገ ቀደም ሲል የትራንዚት ፈቃድ የተሰጠባቸውን የምግብ ሸቀጦች በሙሉ አጠቃሎ ወደ ሀገር ማስገባቱን ከሲስተም ሲረጋገጥ፤

Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
No.2

6. የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚፈልጉ አስመጪዎች ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት በማቅረብ ፈቃድ እንዲያገኙ እና ይሄው በጽ/ቤቱ ፈቃድ የተሰጠበት ደብዳቤ በሚመለከተው የጉ/ቅ/ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ በኩል ታውቆ አገልግሎት እንዲሰጥና በየሳምንቱ የአፈጻጸም ግምገማ እንዲካሄድ፤ የጉ/ቅ/ጽ/ቤቶችም አባሪ በተደረገው ቅጽ መሠረት አፈጻጸሙን ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀን ሪፖርት እንዲያቀርቡ፤ ዳይሬክቶሬቱም መረጃውን በማደራጀት በየወሩ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት እንዲያቀርብ፤

7. ቀደም ሲል የገንዘብ ሚኒስቴር በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ላይ በቁጥር ማኢ.30/7/1431 ነሃሴ 28 ቀን 2013 ባስተላለፈው የቀረጥና ታክስ ማሻሻያ ውሳኔ መሠረት የምግብ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ለማስገባት ዲክለር አድርገው እስከ 02/08/2014 ድረስ በኢትዮጵያ የጉምሩክ መግቢያ በር በኩል ወደ ሀገር የገቡ የምግብ ፍጆታዎች በዚሁ በተሻሻለው የቀረጥና ታክስ ምጣኔ መሠረት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ፤ ከዚህ ውጭ ቀደም ሲል ግዥ የተፈጸመባቸው የምግብ ሸቀጦችም ቢሆኑ የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ከ03/08/2014 ጀምሮ በጉምሩክ የመግቢያ በር አቋርጠው ወደ ሀገር የሚገቡ ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ዱቄት ወተት እና ሩዝ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀደም ሲል በ22/03/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ.30/7/51 ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም እያሳሰብኩ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳወቀበትን ደብዳቤ 04 እና ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ 01 ገጽ በድምሩ 05 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሙሉጌታ በየነ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር
ተወካይ

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለገንዘብ ሚኒስቴር
- ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>።

No.2
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ሪሚኢ30/7/5302
Ref.No
ቀን 30/7/2014
Date

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመሠረታዊ ሸቀጦች ቀረጥና ታክስ ይመለከታል</u>፤

በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ወተት እና ሩዝ ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) ለስድስት ወራት ምንጩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እየተረጋገጠ እንዲገቡ በቀን 7/8/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/108 በተጻፈ ደብዳቤ መፈቀዱ ይታወሳል፡፡

በአሁኑ ጊዜ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት እንዲቻል እና በርካታ የውጭ አገር የመኖሪ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን አዎንታዊ ሚና መጫወት እንዲችሉ የፍራንኮ ቫሉታ ፈቃድ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የህጻናት ወተት እና ሩዝ ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እየተፈቀደ እንዲገባ በመንግስት ተወስኗል፡፡ ቀረጥና ታክስሉን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/3/2013 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም፤ አፈጻጸሙን በሚመለከት በሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፡-</u>

ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ 251-11-155 24 00, 22 66 98 / 251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.BOX 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

ቁጥር 2 No.2
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 4 | 1512.2910 | 5% |
| 5 | 1513.1910 | 5% |
| 6 | 1513.2910 | 5% |
| 7 | 1514.1910 | 5% |
| 8 | 1514.9910 | 5% |
| 9 | 1515.1910 | 5% |
| 10 | 1515.2910 | 5% |
| 11 | 1515.5010 | 5% |
| 12 | 1515.9010 | 5% |
| 13 | 1516.1010 | 5% |
| 14 | 1516.2010 | 5% |

2. ስኳር ላይ ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/73 የተላለፈው ተሸሮ አንደኛ መደብ ታሪፍ መጣኔ (ልክ) ከታች በሠንጠረዥ በቀረበው መሠረት ተሻሽሏል፡-

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 1 | 1701.1200 | 5% |
| 2 | 1701.1300 | 5% |
| 3 | 1701.1400 | 5% |

3. በሕፃናት ዱቄት ወተት ላይ ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር ማኢ30/7/73 የተላለፈው ተሸሮ አንደኛ መደብ ታሪፍ መጣኔ (ልክ) ከታች በሠንጠረዥ በቀረበው መሠረት ተሻሽሏል፡-

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 1 | 0402.1000 | 5% |
| 2 | 0402.2100 | 5% |
| 3 | 0402.2900 | 5% |
| 4 | 0402.9900 | [illegible] |

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Customs Commission Records & Documentation No.2

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ____________
ቀን
Date ____________

| ተ.ቁ | ጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር | ታሪፍ መጣኔ |
|---|---|---|
| 5 | 0402.9900 | 5% |
| 6 | 1901.1000 | 5% |

ስለዚህ ከላይ የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ የተደረገባቸው ታሪፍ ቁጥሮች ከሱር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ ነፃ መሆናቸውን እየገለጽን፣ ከላይ በቀረበው መሰረት ማሻሻያው ከህዳር 23 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተቀባይነት በሚያገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ ተግባራዊ እንዲደረግ ተወስኗል።

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ
- ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  ገንዘብ ሚኒስቴር

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1
Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
No.2

